# ፕሮፌሰሩን የተጠናወታቸው የሙት መንፈስ

**ሰለሞን ሽፈራው 05/13/13**

በመላው የሀገራችን ህዝቦች ያላሰለሰ ትግል ተንኮታክቶ ወደ ከርሰ መቀብሩ የወረደውን የግዛት አንድነት ከመናፈቅና ለሙት መንፈሱ ጥብቅና ከመቆም ቦዝነው የማያውቁት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ከጥቂት ወራት በፊት ባሳተሙት አንድ መጽሐፋቸው የኢትዮጵያ ታሪክ "መክሸፉን" ነግረውናል፡፡

በህዳሴ ጉዞ ላይ የምትገኘውን ሀገራችንን መልካም ገፅታ ለማበላሸት ሲባል ‹‹መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ›› የተሰኘ አወዛጋቢ ርዕስ የተሰጠው የፕሮ ፌሰሩ መጽሐፍ ከታሪክ ድርሳንነት ይልቅ ፅንፈኛ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያካሒዱትን የጥላቻ ፖለቲካ መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ማኒፌስቶ ሆኖ ያገኙት እጅግ በርካታ ዜጎች አዛውንቱን ፕሮፌሰር አምርረው የሚሸነቁጡ ትችቶችን በተለያዩ ሚዲያዎች አማካኝነት ሲሰነዝሩ መሰንበታቸውም የሚዘነጋ አይደለም፡፡

ፈጣሪ ያደላቸውን የዕድሜ ፀጋ፣ ሳይማር ላስተማራቸው ሀገርና ወገን የሚበጅ ሰናይ ተግባር በመፈፀም ያሳልፉት ዘንድ የሚመክራቸው ሁነኛ ወዳጅ ዘመድ ያጡ የሚመስሉት ፕሮፌሰር መስፍን ከመጀመሪያው ስህተታቸው በመታረም ፈንታ ይሄውና ለ‹‹ክሽፈት›› ማኒፌስቷቸው ተፈፃሚነት ግንባር ቀደም የአፈ ቀላጤነት ተልዕኮውን በመወጣት ላይ ወደሚገኘው የሽብርተኞች ልሳን (ኢሳት) አሻግረው እያማተሩ ዕኩይ ምግባሩን እንደ መልካም ነገር ሲያወዳድሱ እያየናቸው ነው፡፡

በእርሳቸው አተያይ ተወቃሽ ያደረጉአቸው ሁልቁ መሳፍርት የሌላቸው ዜጎችን አንድ ላይ ጨፍልቀው ይህች ምስኪን ሀገርና ሕዝቦቿ አንዳች ይቅርታ የማያሰጥ ክፉ በደል የፈፀሙባቸው እስኪመስል በኢትዮጵያ የህዳሴ ጉዞ ላይ እንዲህ በመረረና በከረረ የጠላትነት ስሜት ጥርሳቸውን እንዲነክሱ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢነት ያለው ይመስለኛል። ዕውን አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ከኢህአዴግና እሱ ከሚመራው መንግስት ጋር ላላቸው አለመግባባት ብቻ ነውን ይሆን ያህል ያቄሙት?

ኢ.ህአዴግ በትግል ውስጥ ተወልዶ በትግል ውስጥ ያደገ የፖለቲካ ፓርቲ የመሆኑን ያህል በረዥሙ የውጣ ውረድ ታሪክ በርካታ የድል አድራጊነት ዕሴቶችን እያካበተ መምጣቱ የማይታበል ሀቅ ነው፡፡

የኢ.ህአዴግ ድርጅታዊ ጥንካሬ ከሚገለፅባቸው የድል አድራጊነት ዕሴቶች መካከል በዋነኛነት የሚጠቀሰው ደግሞ ከህዝባዊነት ባህሪው የሚመነጭ የዓላማ ፅናትና የትግሉን ሒደት ከየወቅቱ አካባቢያዊ (ሀገራዊ) እና ዓለም አቀፋዊ እውነታዎች ወይም የሃይል አሰላለፍ ጋር እያገናዘበ የመቃኘት (የመምራት) ፖለቲካዊ ብቃት እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል ብዬ አምናለሁ፡፡

በ1983 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ የተካሔደው የኢ.ህአዴግ 1ኛ መስራች ጉባኤ የወቅቱን አጠቃላይ እውነታ ከሀገራችን የፖለቲካ ሃይሎች አሰላለፍ አኳያ ሲገመግም፣ ከደርግ ውድቀት በሁዋላ በምትኖረው ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ጉዞውን ለማስቀጠልና ላለማስቀጠል በሚፈልጉ ሃይሎች መካከል ሊደረግ የሚችለውን እልህ አስጨራሽ ትግል አስቀምጦ እንደነበር ይታወሳል።

የያኔው ግምገማ ፍሬ ሀሳብ ‹‹ከደርግ ውድቀት በሁዋላ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች የሚያካሒዱትን ሰላማዊ ትግል በመፈታተን ረገድ ለወደቀው ስርዓት ጥብቅና ከመቆም የማይቦዝኑ ትምክህተኞች አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ ድርጅታችን ከወዲሁ ተገንዝቦ አስፈላጊ ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል››የሚል ሲሆን እነዚህ ኅታች አመለካከቶች የለውጥ ሒደቱን ከማደናቀፍ አኳያ የሚኖራቸውን ገፅታም ከነምክንያቱ አብጠርጥሮ ነው ያስቀመጠው፡፡ እጅግ በጣም የሚገርመው ደግሞ ኢ.ህአዴግ በዚያ ታሪካዊ መስራች ጉባዔው ግምገማውን ያሰፈረበት ፊርማ ገና በቅጡ እንኳን ጠፈፍ ሳይል ነበር የአንባገነኑ ወታደራዊ መንግስት ግብዓተ መሬት የተፈፀመው ፡፡

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢ.ህአዴግ) በመስራች ጉባዔው የተወሰኑትን ድርጅታዊ ውሳኔዎች መሰረት አድርጎ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የለውጥ ትግል ግቡን እንዳይመታ ዋነኛ ምክንያት ሆኖ የቆየውን የደርግ አንባገነናዊ ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የመደምሰስ እንቅስቃሴውን በታሪካዊው ወርሀ የካቲት 1983 ዓ.ም. ‹‹ዘመቻ ቴዎድሮስ›› በሚል የዘመቻ ስያሜ ስትራቴጂካዊ የማጥቃት እርምጃውን ጀመረ።

ይህ ሁኔታ ከመቸውም ጊዜ በላይ የሚይዙ የሚጨብጡትን ያሳጣቸው የደርግ ኢሰፓ ቁንጮዎችም ‹‹የ17 ዓመታት ትራጀዲ ተውኔታቸውን የመጨረሻ ክፍል የተጫወቱበት የጣረ ሞት ትንቅንቅ›› ሊባል በሚችል መልኩ ይህችው የፈረደባት ድሀ አገር የዕውቀት ብርሃን

አይተው እንዲያሳዩዋት ስትል ቀለብ የምትሰፍርላቸውን በሺህ የሚቆጠሩ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ለጦርነት እሳት ለመዳረግ ተንቀሳቀሱ። ገና በቅጡ እንኳን ሳይሰለጥኑ ኮለኔል መንግስቱ ሃይለማሪያም ራሳቸው ከብላቴ የማሰልጠኛ ካምፕ አግበስብሰው አመጡና ወጣቶቹን ከተፋፋመው የጦርነት እሳት ውስጥ ለመማገድ አዘጋጅተዋቸው ወደ ቤተ መንግስታቸው ተመለሱ፡፡

ኮለኔሉ በወቅቱ ‹‹እናት ሀገራችሁ ኢትዮጵያ የመጨረሻ ተስፋዋን በእናንተ ላይ ነው የጣለችው፣ ስለዚህም እንደማንኛውም ዜጋ የማትቆጠሩ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች እንደመሆናችሁ መጠን ሳይማር ላስተማራችሁ ህዝብ ነፃነት ስትሉ ይህን ከጫካ የመጣ የወንበዴ መንጋ ልኩን አሳውቃችሁ እንደምትመልሱትና ሀገራችሁን ከመገነጣጠል አደጋ በመታደግ መንግስታችንን እንደምታኮሩት ቅንጣት ያህል አልጠራጠርም!!›› የሚል ዲስኩራቸውን አሰምተው እንደነበረም ይታወሳል፡፡

እንግዲህ ይህ ከሆነ ከአንድ ወር በሁዋላ ነው ፕሬዚዳንት መንግስቱ የብሔራዊ ሸንጎ አባላትን ለአስቸኳይ ስብሰባ በአዲስ አበባ ለመጥራት የተገደዱት፡፡ በዚያ የሰዓታት ዕድሜ በፈጀና ምናልባትም ‹‹የንግግር ማራቶን›› ሊባል በሚችል ረጅም ኑዛዜያቸው ፕሬዚዳንት መንግስቱ በዚች ሀገር ሕዝቦች ፊት ከደፈሩአቸው መራር የታሪክ እውነታዎች መካከል የሰራዊታቸውን ወኔ ቢሲነት ያውም ለሰሚው በሚቀፉ ፀያፍ ቃላት የገለጹበት የጣዕረ ሞት ንግግራቸው ነበር፡፡

ኮለኔል መንግሥቱና አጫፋሪዎቻቸው ‹‹ገበሬ›› ያሉት የኢህአዴግ ሰራዊት ያሸነፉቸው ባለው የአላማ ፅናት እንጂ በሌላ ምክንያት እንዳልሆነ ኮለኔሉ እግረ መንገዳቸውን ያረጋገጡበት አጋጣሚም ነው ያ ንግግር፡፡

ሚያዝያ 9 ቀን 1983 ዓ.ም.የተካሄደውን የደርግ ምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ ማንሳት የፈለኩበት ዋነኛ ጉዳይ ግን፣ በወቅቱ ስብሰባውን ለመጥራት ምክንያት ስለሆነው የባለአደራ መንግስት የማቋቋም ጥያቄ ፕሬዚዳንት መንግስቱ ራሳቸው ባቀረቡት የመፍትሔ ሃሳብ፣ ለፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም ያሳዩት ወገንተኝነት ለማሳየት ነው፡፡

የኢህአዴግ ሰራዊት ግስጋሴ፣ እዚህ… አምቦ ድረስ ገፍቶ መምጣቱን የተረዱት ኮለኔሉ በፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም ፊታውራሪነት ከሀገሪቱ ታዋቂ ምሁራን ለሚዋቀር የባለ አደራ መንግስት ስልጣናቸውን የማስረከብ ሀሳብ ማቅረባቸው የሚታወስ ሲሆን፣ በወቅቱ ሃሳቡን

አምርረው ከተቃወሙት የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት ኢህአዴግ ዋነኛው እንደነበረም አይዘነጋም፡፡

ፕሮፌሰሩ በ1967ቱ ግብታዊ አብዮት ምክንያት የተፈጠረውን ንግግር ተጠቅመው የፖለቲካ ስልጣን የጨበጡት ጥቂት ወታደሮች ገና ከመነሻው የአፄ ሃይለስላሴ መንግስት የካቢኔ ሚኒስትሮች፣ ያለምንም የፍርድ ሒደት በጅምላ ግድያ እንዲረሸኑ በማድረግ ረገድ እጃቸው አለበት ተብሎ እንደሚታመን የጠቆመው የኢህአዴግ ተቃውሞ፣ ‹‹ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ባለችው ኢትዮጵያ ውስጥ ደርግ የፈፀመውን አረመኔያዊ ተግባር ሁሉ፣ አይተው እንዳላዩ ሲያልፉ ወይም በቸልታ ሲመለከቱ የቆዩትን ፕሮፌሰር መስፍንን ስብሰባው ላይ ለተነሳው ጉዳይ ወዲያውኑ ማጨት በራሱ ኮሎኔሉና ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ለህዝቡ ያላቸው ንቀት ገደብ ማለፉን ያመለክታል።

በእርግጥም ደግሞ ይህች ምስኪን ሀገር በነፍሰ በላው የደርግ መንግስት ቁንጮ አንባገነኖች ‹‹የነፃ እርምጃ›› መቅሰፍት ወርዶባት ‹‹የቀይ ሽብር›› ሰለባ በሆኑ ንጹህን ዜጎቿ ደም ስትጨቀይ፣ እንደሰው ወግ ማዕረግ ለማየት ወልደው ያሳደጉ እናቶች የወጣት ልጆቻቸውን በድን አካል (ሬሳ) በገንዘባቸው እንዲገዙ ሲገደዱና ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር ከል ስትለብስ እዚችው አዲስ አበባ ውስጥ ተቀምጠው ይመለከቱ ለነበሩት ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም የሊቀ መንበር መንግስቱን ስልጣን ለማውረስ መታሰቡ ታላቅ ንቀት ነበር፡፡

ካለፉት 22 ዓመታት ጀምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰፊ መሰረት እየያዘ የመጣውን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ተከትሎ በዚች ሀገር የፖለቲካ ባሕል ያልተለመደ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ የትግል ስልት መከተል ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነበርና በየጊዜው መልካቸውን እየቀያየሩ ይህን አዲስ ዴሞክራሲያዊ ሥርአት ሲፈታተኑት የሚስተዋሉትን የትምክህተኝነትና የጠባብነት ኋላ ቀር አመለካከቶች በመታገል ለማምከን ኢሕአዴግና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፈርጀ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል።

ከስርዓት ለውጡ ዘላቂ ጉዞ አኳያ ሊያሳድሩ የሚችሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ በተመለከተ፣ ሲገመግም ከነሱ ጋር የሚደረግ ትግል፣ የሚኖረውን ውስብስብ ባህሪ ጭምር ጥርት ባለ ሁኔታ ማስቀመጡም ያለምክንያት እንደአልነበረ፣ በድህረ ደርግ አትዮጵያ የገጠሙንና አሁንም ድረስ እየገጠሙን ያሉ ፈተናዎች በቂ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ ለሰላማዊ ትግል ባዕድ ሆኖ በኖረው የኛ ሀገር ፖለቲካ ውስጥ የአንድ ወገን ሆደ ሰፊነት ብቻውን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባት ጥረቱን ምሉዕ እንደሚያደርገው ግን ኢህአዴግና አጋሮቹ ሕገ መንግስታዊ ሒደቱን ላለማስቀልበስ ሲሉ እስከ ዛሬ ከተጋፈጡት እውነታ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

እነሆ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ታሪክ ጎላ ጎላ ብለው የተስተዋሉ ጋሬጣዎችን ከመዳሰስ አኳያ ቀዳሚውን ስፍራ ከሚይዙ የጠባብ ብሔርተኝነት ሰለባዎች ዋነኞቹ ደግሞ ራሱን ‹‹የኦሮሞ ነፃነት ግንባር›› እያለ የሚጠራው ኦነግና ‹‹የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር›› (ኦብነግ) የተሰኘው ቡድን ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

መገንጠልን እንደብቸኛ አማራጭ የመቁጠር አባዜ ተጠናውቷቸው በስርዓት ለውጥ ሒደቱ ላይ ነፍጥ እስከ ማንሳት የደረሱት እነዚህ ጠባብ ቡድኖች ገና ከሽግግሩ ወቅት ጀምሮ የፈጠሩት ችግር ታሪክ ይቅር የማይለው ቢሆንም፣ መላው ኢትዮጵያ ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው በጀመሩት የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ ፌዴራላዊ ስርዓታችን ስር እየሰደደና የትሩፋቶቹ ተደራሽነትም በዚያው ልክ እያደገ በመጣ ቁጥር ጠባብነት እንደአመለካከት ማንንም ለትግል ሊያሰልፍ ወደማይችልበት ደረጃ እየከሰመ እንደሚገኝ ግን የሚያከራክር አይሆንም፡፡

በያኔው የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባዔ፣ ከደርግ መንግስት ውድቀት በሁዋላ በምትኖረው ኢትዮጵያ የሚከፈተውን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ወይም ስር ነቀል የስርዓት ለውጥ ሒደቱን ለማስቀጠልና ላለማስቀጠል ሲባል ሊደረግ የሚችለውን ሰላማዊ ትግል አስመልክቶ ሲገመግም፣ በተለይ እንዲህ እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ዓይነቶቹ፣ ለግዛት አንድነት የሙት መንፈስ ጥብቅና ከመቆም የማይቦዝኑና ከቶውንም ሽንጣቸውን ገትረው ሊከራከሩለት የሚደፍሩ ትምክህተኛ ምሁራን የሚያራምዱት አስተሳሰብ፣ የህዝባዊ አብዮቱ ዘላቂ አደጋ መሆኑ እንደማይቀር፣ በአንክሮ ማስገንዘቡንም የምንዘነጋው ጉዳይ አይደለም፡፡

እነዚህ የወደቀው ስርዓት ርዝራዦች፣ መገንጠልን ቀዳሚ ምርጫ አድርገው ከሚወስዱት ጠባብ ብሔርተኞች የሚለዩበት መሰረታዊ ባህሪ፣ ትምክህተኞች ‹‹በሁሉም ነገር ከኛ ወዲያ ለአሳር ነው›› የሚል የመታበይ ልክፍት የተጠናወታቸውና እነሱ በማይገዙባት ኢትዮጵያ የወርቅ ምንጣፍ ቢነጠፍላቸው እንኳን ለአዲሱ የታሪክ ምዕራፍ መልካም ገጽታዎች ዕውቅና መስጠትን እንደ ውርደት ስለሚቆጥሩት፣ መቸም ቢሆን የግዛት አንድነትን ከመናፈቅና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የስርዓት ለውጥ ሒደቱን ለ‹‹ማክሸፍ›› (ለማምከን) ከመሞከር የማይቆጠቡ ለመሆናቸው ተግባራቸው በግልጽ ያመለክታል።

አንባገነናዊው የደርግ ስርዓት በመላው የሀገራችን ህዝቦች የዘመናት ትግል ተወግዶ የአዲሲቱ ፌዴራላዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ምስረታ ዕውን ከሆነበት የግንቦት ሃያው ታሪካዊ ድል ጀምሮ፣ ዲሞክራሲያዊ የለውጥ ሒደቱን ‹‹ውግዝ ከምአሪወስ›› በሚል ጭፍን ተቃውሞ ከማጥላላትና በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ለመቀልበስ ያስችለናል ያሉትን ሴራ ከማውጠንጠን ቦዝነው

ከማያውቁት የትምክህት ሃይሎች በስተጀርባ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያምና ያረጀ - ያፈጀ የ‹‹ክሽፈት ፍልስፍናቸው›› እንደነበሩበት ደግሞ ፀሐይ የሞቀው እውነት ነው፡፡

ለዚህም በ1993 ዓ.ም.ሁለተኛውን አገርአቀፍ ምርጫ የማወክ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ተደርሶባቸው በሕግ ቁጥጥር ስር ከዋሉትና ወደ ሸዋሮቢት ማረሚያ ቤት ተወስደው ለአጭር ጊዜ በእስር ከቆዩ ጥቂት የተቃዋሚ ፖለቲከኞች አንዱ ፕሮፌሰሩ እንደነበሩ ማስታወስ ይቻላል፡፡ በተለይም የ1997ቱን አገርአቀፋዊ ምርጫ ተከትሎ ተቃዋሚዎች እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ባካሄዱት ሕገመንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ ያለመ የአመፅ ተግባር ምክንያት፣ ለደረሰው የህይወትና የንብረት ጥፋት ተጠያቂዎች መሆናቸው በፍርድ ቤት የክስ ሒደት ተረጋግጦ፣ የዕድሜ ልክ እስራት ከተበየነባቸው በሁዋላ በፈፀሙት ስህተት መፀፀታቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ ለመንግስት ስለፃፉ ይቅርታ ተደርጎላቸው በነፃ ከተለቀቁት ‹‹የቅንጅት›› ነውጠኛ አመራር አካላት መካከልም አንዱ እርሳቸው እንደነበሩ እዚህ ላይ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡

እርሳቸው ግን እስከዛሬ በፈፀሙት ድርብርብ ጥፋት ቅንጣት ያህል ፀፀት እንደማይሰማቸው ከጥቂት ወራት በፊት ባሳተሙት የክሽፈት ድርሳናቸው አረጋግጠውልናል፡፡ በዚህ ጽሑፋችን መግቢያ ላይ እንደተመለከትነውም አዲሲቷ ኢትዮጵያና መላው ህዝቦቿ የተያያዙትን የለውጥ ጉዞ ለመቀልበስ ታጥቀው የተነሱት እነ ‹‹ግንቦት ሰባት›› የሽብር ፈጠራ አጀንዳቸውን ለማስፈፀም የሚጠቀሙበትን ‹‹ኢሳት›› የተሰኘ የሚዲያ ተቋም ሲያወድሱ ትንሽ እንኳን አላፈሩም ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም፡፡

ከፊርጀ ብዙ ድህነት ጋር የሞት ሽረት ትግል እያደረገች ላለችው ሀገራቸው የልማት ተግባር የሚውል ገንዘብ ለማሰባሰብ የፈለጉ ዳያስፖራ ኢትዮጵያዊያን የሚጠሩትን ስብሰባ መቃወምና እንዲቋረጥ ማድረግ የለየለት የሀገር ክህደት ነው እንጂ በየትኛውም መመዘኛ ውዳሴ የሚቸረው የፖለቲካ ትግል ሊሆን አይችልም፡፡  እናም ፕሮፌሰሩ ሆይ እዚህ ላይ ትንሽ ቆም ብለው በጽሞና ማሰብ የለብዎትምን?